# ህወሓት፡የአንድነት ጉዞውና መፍትሄው

ኢህአደግ እንደመንግስት ኢትዮጵያም እንደሃገርየመቀጠሉ ጉዳይ ከባድ ፈተና እየገጠመዉ ነው።. ለጊዜዉም ቢሆን። ለችግሩ ዋና መንሰኤ ደግሞ የኢሃዴግ አመራርና የአሰራርችግርነው። ከፊሉ በነግ ይደረሳል፡ ከፊሉ በየት ይደረሳል ፡ ከፍሉ ደግሞ በተደርሷል በየፊናዉ በራሱመላ ምትና እምነት እየተመራ ነጠላ መንገድን ይዞ በትናጠል በመጓዙነው። አባል ድርጅቶቹ የግልንና የቡድንን ጥቅም ለማስቀደም ሃገርንና ህዝብንለሰቆቃናለችግር በመዳረጋቸው ነው። ቡድናዊ የበላይነት ለመጨበጥ የህብረት እናየአንድነት መንገዱን ከመሸርሸር አልፈውአንዱ በሌላዉ ላይ ያተኮረ የመጠቃቃት ዘመቻ በመጀመራቸው ነው። ከመተራረም ይልቅ አንዱ በሌላው ጥፋት ጎልብቶ ለመዉጣትበማሴር ተግባር የተጠመዱ ስለሆነ ነው።በማን አህሎኝነት ህጉናን በትረ ህጉን የግል ይዞታቸው ለማድረግ እራሳቸው ላወጡት ህግም አልገዛም በማለታቸው ነው። ይህ የመጠፋፋት መንገድ፡ ይህ ሽኩቻ እና የስግብግብነትመንገድ ለህዝቡም ተርፎ ወደ እርስ በርስ ግጭትእያመራዉ ይገኛል። እዚህም እዛም ብቅ ጥልቅ የሚለው ድርጅትና ክልል ተኮር ግጭት የዚሁ ዉጤት ነው።

ግጭቱን ለማብረድ መንግስት የአስቸኳይ ግዜ አዋጅ አዉጇል። የተለያየ እርምጃወስዷል። እየወሰደም ነው። እሳቱየመጥፋቱ ነገር ግን ያጠራጥራል። ምክንያቱም በስተጀርባ ሁኖየህዝቡን ችግር እንዲባባስ ቤንዚን በማርከፍከፍ ላይ ያለው መንግስት ( በስነምግባሩ)ወይ ደግሞ የመንግስት አባል ድርጅት(በተንኮሉ)ነው። በታሪክ የምናውቀው ህዝብ ወይ ተቃዋሚ መንግስትን ሲቃወም ወይ ሲገለብጥ ነው። የኢህአዴግ ግን ለየት ይላል። ገልባጩምተገልባጩምራሱ መንግስት ነው።ህግ ደንጋጊውህግ አፍራሽም እራሱ ነው።ገላጋዩም ድንጋይ አቀባዩም እራሱ መንግስት ነው።ከህብረቱ ይልቅ መትናኮል ነው የሚበዛበት። ስለ ህዝብ ተብሎ ግን አይደለም። ክርክሩ የክልልን ህዝብ መብት አስከብሮ የሌላዉ ክልል ቀረከሚል አይደለም። የሚያክልውን ይዞም የአነሰኝ ነው። የሌላውን ጥቅም ለምን እኔ አልወሰድኩም ነው። ብቃት አለው የለዉምምሳይሆን ከሌላው ክልል ለምን ተመደበ ነው። ስልጣን በማን እጅ አለ: ለየትኛው ክልል ተወላጅ ተሰጠ ነው። ባጭሩ መንስኤው የስልጣን አምሮት ነው። እንድትጠፉ በወሰኑላት አገር የአገር የበላይ አስተዳዳሪ (አጥፊ እንበለው) መሆን ነው።

የችግሩ መስቀል ተሸካሚ ሆኖ ያለው (በአመልካከቱ ወይ በብሉሹነቱ ወይ በተቀናቃኝነቱ አለያም በሞኝነቱ) ህወሓት ነው፡፣ የበላይ ሆኖ በድርጅትና በክልል ጉዳይ ላይ ጣልቃ እየገባ አላሰራም አለ ተብሎ።ህወሓትም ቢሆን በበኩሉ የሚከሰው አላጣም። በድለዉኛል የሚላቸው ድርጅቶች አሉት።ሁሉም ከሳሽ፡ ሁሉም ተከሳሽ ነው። ጣት መቀሳሰሩ ማቆምያ አለው?መልሱ አዎን ነው። አንደኛዉ ህዝቡ የመብት ባለቤት ሲሆን ነው። ይህ ግን አሁን አይታሰብም ምክንያቱም ገኖ ያለው የህዝቡ ህብረትና አንድነት ለያይ ሃይል ነው። ሁለተኛዉ ደግሞ ድርጅቶቹ ሰላማቸውን ሲፈጥሩ ነው። ይህ ይቻላል። ችግር ቢኖረዉም ልብ ብቻ ነው የምጠይቀው።ልቡን ደግሞ ከገበያም ቢሆን መግዛት አለባቸው። ለህዝብ ብለው ሳይሆን ለራሳቸው። ምክንያቱም ስለበደሉት ሳይሆን ስለሚበሉት እናስላ ከተባለ ከግጭቱ ይልቅ ሰላሙነው የሚጠቅማቸው።ለሃብት እና ለስልጣን ሲሉ የገደሉ ግን ደግሞ ሃብትና ስልጣን የገደላቸው እንደ ጋዳፊ እንደ ሳዳም ሁሴን ሊሆን ስለሚችል እጣቸው። መቼም ኢትዮጵያ ለህዝቧ ገሃነም ሆና ድርጅቶቹ በተለየ አይደላቸው። ምክንያቱም ለኢትዮጵያ በደገሱላት ጥፋት እነሱም ጠፊዎችናቸው። ስለዚህ የእልህ ስራ አቁመው የህብረቱን ስራ ነው ማስቀደምና መተግበር ያለባቸው። ይሄው ነው የሚያዋጣችው ።

ይህን ለመተግበር ደግሞ የውጭ ሽምጋይና ገላጋይ አያስፈልጋቸውም።፣ ህዝባቸውን አማክረዉ የሚበጀውን መወሰን ነው። የመጭዉን ማሰብ ነው። አልሆን ካለ ደግሞ ስልጣን ለህዝብ ማስረከብም አለ። ይሄም አማራጭ ነው። በደንብ ሊታሰብበት የሚገባ። በዚህ ሂደት የህወሃት ሚና ምን መሆን አለበት? አፍራሹ ማን ሆነና ነው አስተካካዩ ህወሃት የሚሆነው ? ብሎ የሚጠየቅ አይጠፋም።መጠየቅም አለበት። ላለፉት ሰላሳ ሁልት(32) አመታት የህወሓትን አመራር( እስከ አለፈው አመት ድረስ የነበረው) በጉንጭ አልፋ ልፈፋ ነበር የሚኖረው። ታድሻለሁ ይልና መልሶ እዛው ጭቃው ላይ ነው። በቅርቡ ጥፋተኛ ነበርኩብሎ አምኗል። እታረማለሁም እያለ ነው። ለስድስተኛ ወይ ሰባተኛ ጊዜ መሆኑ ነው። በቃሉ ጸና አልጸና ነጌ የሚታይ ነው። እስከዛው ድረ ግን ጥሩውን እንመኝ። አይኾንን እንተበላ አዴኺየ ይኾን እዩ በልየን ባዕልኺየ (አይሆንም ቢሉሽ እናትሽ አንቺው ራስሽ ይሆናል በያቸው) ተብሎ እንደተዘፈነው። ከታረመ ደግሞ በአንድነት ጉዞዉ በመቀጠሉ ጉዞ ትልቅ ሚና ሊጫወትይችላል። አቅምም አለው ። መጫወትም አለበት። የከአሁን በኋላ ጥፋት ፡ የከአሁን በኋል አለመታረም ለጥፋቱ

ነው። እናም የሚበጀው ነገሮች ሳይበላሹ ማስተካከል ነው ። የመፍትሄው ችግር ሳይሆን የችግሩ መፍትሄ (ከልብ ካለቀሱ እንባ አይገድምና ) መሆን ነው። የዚህ ጽሁፍ ትኩረትም ይህን ማስተጋባት ነው። መፍትሄ ያላቸውን መጠቆም ነው። መልካም ንባብ።

ጥፋተኝነቱ የሚጀምረው ከህወሓት ነው ካልን መፍትሄዉም መጀመር ያለበት ከህወሓት ቤት ነው፡፣ እሱም ደግሞ የሚጀምረው የራስን ቤት በማጽዳት ነው። ቤቱ የሚጸዳ ከሆነ ደግሞ መጀመር ያለበት በሙስና የተጭማለቁ አባላቶቹ ላይ የጽዳት ዘመቻ በማካሄድ ነው። የራሱ ጅቦች ሸሽጎ ቀበሮዎቹን ማሳደድ ትርፉ ትዝብት ነው። በትግራይ ይሁን በተቀረዉ የኢትዮጵያ ህዝብ ዘንድ ተኣማኒነት የሚኖረዉ በክልሉ የተሰገሰጉ  መዥገሮችን መነጥሮ ያወጣ እንደሆነ ነው። የእከከኝ ልከክልህ  ትስስር በጥሶ ብህዝብ ጫንቃ ላይ የተጠመጠሙት ዘንዶዎችያስወገደ እንደሆነ ነው። በግል ንብረትነት የተያዙት የህዝብ ተቋማትን ለህዝቡ አገልግሎት የሚዉሉበት መንገድ ያበጀ እንደሆነ ነው። ጊዜ ተቅይራል። ህዝብ አምርሯል። ይህ ደግሞ ለነገ የሚባል አይደለም። ክሃገርና ከህዝብ በላይ የለም ከተባለየሚሻለው ክሙሰኞች ጋር ያለን ዝምድና ላላ አድርጎ ክህዝብ ጋር ያለውን ጠበቅ ማድረግ ነው። በፍትህ እጦት የሚንገላታዉን ህዝብ መታደግ ነው። ጎራን ለይቶ ከወንጀሉ ጽድቶ ህዝቡን ከወንጀለኞት ነጻ ማዉጣት ነው። በጥፋት ላይ ከመክራከርና ከመደራደር ይልቅጥፋትን ኣምኖ ቀናዉንና ህዝብ የሚወደውን መተግበር ነው።

ጋንዲ ያለዉን ልብ ይሏል። ነገሩ እንዲህ ነው። እናት ልጇ ስኳር እየቃመ አስቸገራትና ይዛው ወደ ጋንዲ ትሄዳለች። ኣባት ስለሆነ እንዲመክርላት ብላ ነው። ችግሯንም ነገረችዉ። ጋንዲም ልጁን ከሁለት ሳምንት ብኋላ ይዛው እንድትመጣ ይነግራታል። ተሰነባብተው ቀነ ቀጠሮዉደርሶ ይዛዉ መጣች።ጋንዲም ልጁን "አንተ ልጅ ስኳር ኣትቃም" ብሎት ዝም ይላል። ምክር መሆኑ ነው። ቁንጥጫና ተግሳጽ ይከተላል ብትል የለም። ብትጠብቅም የሚታሰብ ነገር አልሆነም። ገርሟት ባቡጂ (ኣባት እንደማለት ነው) ምነው ያኔ የመጣሁ ጊዜ ይህን ማለት እየቻልክ ሁለት ሳምንት ቀጠርከኝ? አለችዉ። ጋንዲም "ያኔማ እኔም ስኳር መቃሙን አልተዉኩም ነበር" ኣላት።ተውማለት ጥሩ ነው: ግን ደግሞ ሚዛን የሚደፋዉ ተው የሚሉትን የተዉ እንደሆነ ነው።ከሚያስነቅፍ ነገር እራስን ያገለሉ እንደሆነ ነው።ጥሩ ስራ ኣተላ የለዉም።ዘግይቶም ቢሆን። የሚሻለው ጥሩ መስራቱን ነው።

የትግራይ ህዝብን ኣስመርሮት ያለዉ የኣስተዳደር ብሉሽነት መፍትሄ ይበጅለት። ከሃያ ኣምስት ኣመታት በላይ  በስልጣን የተዛመዱና የተሳሰሩ ቡድኖች በይ ህዝቡ ደግሞ የነሱ ተመልካች ሆኖ ነበር የቆየው። የኣንድን ወገን  (ቤተሰብ እንበለው እንጂ ) ጥቅም ብቻ ያስጠበቀን  አሰራርር ነበር ሲተገበር የነበረው።ለኣለም ይተርፋል የተባለው ጥጃ ተጠምዶ የቀረው በዘር ሃረግ ቆጠራ ነው። ማንበክዚህ ወይም ከዚያ ኣውራጃ ተወለደ ነው።  ከዚህ ኣውራጃ ከሆንስ ዘመድ ነው ወይስ አይደለም ነው። ዘመድ ከሆነም ኣምስት ወይም ሰባት ደረሷል አልደረሰም? ነው።ባጭሩ ህዝቡ ነጻ ያወጡኛል ብሎ ተስፋ በጣለባቸው ኣመራሮች ብዙ ተበድሏል። ፍትህ ኣጥቶ ተንገላቷል። ጉቦ ከፍሎም አልሆነ ብሎታል። የቀረው በቁሙ መቀበር ነው። ኣድልዎዉ  ይብቃ፡ ፡ ኣዉራጃዊነቱይብቃ። በህዝብ ስቃይ ኪስ ማሳበጥይብቃ። ያስገኘው ትርፍ ቢኖር የትግራይ ህዝብን ኣንድነት መሸርሸር ነው።ይህን ለማቆም ደግሞ ደግሞ ሳይንስ አይደለም የሚፈልገዉ። ቅን ልቦና ነው። አዙሮ ማየትን ነው። ቁርጠኝነት ነው። "ሕጂ ዶ ይሐይሽ ደኒንካ ምብካየ ቐደም ነበረ እምበር ፈሰስ ምንካየ" ተብለው ናኩራ ከትስደዱት ከነ ደጃዝማች ተሰፋይ ታሪክ ትምህርት መቅሰም ነው።

በትግራይ ክልል እስር ቤቶች ታጉረው ያሉ እስረኞችም ይፈቱ።በነባሩ የህወሓት ኣመራር ዘንድ የተሰረቀ በግና የትግራይ ህዝብ እኩል ነበር የሚታዩት። ሲያሻቸው የሚያስሩትና የሚገድሉት፡ሲያሻቸው ለገጸበረከት ወይም ለገንዘብ ኣሳላፊው የሚሰጡት ። ሻእብያን ለማስደሰት ትግራዩን ማሰርና ማሳሰር፡ ኦነግን ለማስደሰተ ትግራዩ ሲገደል ዝም ማለት፡ የኣማራ ክልል ተቃዋሚን ለማስደሰተ ትግራዩ እየተበደለ ዝም ማለትየሁሉጊዜ ስራቸው ነበር።የህወሓት ከፍተኛ ኣመራር (ነባሩ)በሌላው ክልልተሰሚነት የሚያስገኝለት ይሁን እንጂ የትግራይን ህዝብ መስዋእት ከማቅረብ ወደ ኋላ ብሎ ኣያውቅም። ይህ መቆም አለበት። ኣመራሩጥፋተኛ ነበርኩ ብሏል። ኣብዛኛዉ እስረኛ ደግሞ በዚህ መጥፎ ኣመራርና ኣሰራር ሰለባ ሆኖ ለእስር የተዳረገ ነው። ኣለጥፋቱ ጥፋት ሰርተሃል ተብሎ የታሰረ ነው። በመሆኑም እስረኛውን መፍታት ዋል እደር ሊባል አይገባም። ባዶ እንዳይሆን ከተፈለገም ኣሳሪዎቹን ማሰር ነው። በሙስና የጨቀዩትን ኣመራሮች ማጎር ነው። ደግሞም በተመሳሳይ ዉንጀላ የታሰሩት

የኣማራዉና የኦሮሞዉ የፖለቲካ እስረኛና ወንጀለኛ እየፈቱ የትግራዩን ማጎር ደግሞ ጥሩ ኣይደለም። የሚያስተላልፈው መልእክት ሌላ ነው።

በኣጋር ድርጅቶቹ መሃል ያለው ኣለመግባባት ፈትቶ የኣንድነት ጉዞ መጀመር ኣለበት። ኢሃኣዴግ ብህብረት የሰጠዉ መግለጫ ከምር ከሆነ መልካም ነው። ኣገር ለማጥፋት ብቻ ሳይሆን ኣገርን ለመብላትም ህብረት ጥሩ ነው። ለሽፍትነት ያቆበቆበ የክልል ድርጅትን ይዞ ህብረቱ ይሰራል ማለት ግን ኣይታሰብም።ዉሎ ኣድሮ ዉጤቱ የተበታተነች ኣገር ነው የሚፈጥረው ።የክልል ባለስልጣናት( ትግራይን ጨምሮ) ከህዝቡ በላይ የሆነ ለህዝብ የማይገዛ ስልጣን ሊኖራቸው ኣይገባም። ያገለገለው ነገር ቢኖር በህዝብ ላይ የሚፈጸም ግፍና ቅጥ ያጣ ሙስና  እንዲሰፍን ማድረግ ነው። ህዝብን ማስመረር ነው። መንግስት ሆኖ በመንግስት ኣልማከልም ማለት ነው። ዮህዴዱ የቅርብ ጊዜ እርምጃ ልብ ይሏል። ይህ እንዲያበቃ ክልልን ኣስታክኮ የሚደረገው ድርጅታዊ የፖለቲካ ድብብቆሹ ጫዋታ ይቁም።ኣገር የሚበትን ህዝብን የሚያለያይ ነው። ኣፍራሽ ነው። ደሮን በቆቅ የሚለዉጥ ነው። ድርጅቶች ሲያሻቸው በበር ሲከፋቸው ደግሞ ብጓዳ እየገቡ ኣገሪቱን እንደመያዣ ሊጠቀሙባት ኣይገባም። ወይ ኣብረው ይስሩ ካልሆነም ቁርጡን ይለይላቸው። ላይተማመኑ ነጋ ጠባ መማማሉ ህዝብን ማስልቸት ነው።

ድርጅቶቹ ተስማሙም ኣልተሰማሙም በሃገር ደረጃ ህግ የሚገዛዉና በህግ የሚገዛ ህብረተሰብ መፈጠር ኣለበት። ሁሉ የሚጠየቅበት ብሄራዊ ህግ ይኑር። ደጋፊም ይሁን ተቃዋሚ ሃይል ህጋዊ ክርክርና ምክክር (ካሁኑ በተሻለ)የሚያደርግበት ሰርኣትምይኑር። ይህች ሃገር የሁሉም ናት።ዜጋዉ እንደማንኛዉም ባለ ስልጣን ሊቆርቆርላት እንደሚችል ህወሓት(ሌሎች ድርጅቶችን ጨምሮ)መረዳት ኣለበት።ስልጣን በህግ ተመርቶ ህግን ለማስከበር  የተሰጠ ወይም የሚሰጥ ዉክልና ነው። ህጉ ዋስትና የሚኖረዉ ደግሞ  ህዝቡና መንግስቱ ለህግ ሲገዙ ፡ ኣተገባበሩን በተመለከተ ኣብረዉ ሲመክሩና ህጉን በተግባር ስያዉሉ ነው። ስለዚህ ህዝቡ ሲያስፈልገው ህጉን ሲያሻው ደግሞ ባለስልጣናቱን በህግ የሚጠይቅበት ህግ መፈጠር ኣለበት። ህዝባችን ህግ ኣክባሪ ነው። የሚፈልገዉ በህግ የሚተዳደርና በህግ የሚያስተዳድረዉ መንግስት ነው። ህወሃትና ኣጋርየሚላቸው ድርጅቶች ህጋዊናበህግ የሚመሩእንዲሆኑ ነው። በጦርነት የተዋጣለት የፈረንሳዩ ናፖልዮን “ዝናየ ገኖ የሚኖረዉ ብብዙ የጦርነት ኣውድማ ተካፍየ በተቀዳጀኋቸው ድሎችሳይሆን ባወጣሁት ህጌ ነው”ያለዉ ያለ ምክንያት ኣልነበረም።ከድሉ በላይ፡ ከስልጣኑ በላይ የህግን የበላይነት፡ የህግን ዘላቂነት በመገንዘቡ ነው።ስልጣን ኣለህግ ዋጋ እንድሌለው ስለተገነዘበ ነው። ህወሓትም ይህንን መገንዘብ ያለበት። ለሰላሙ መሰረቱ  ህግ ነው።

ይህ እንዲሆን ደግሞ የመንግስት ኣወቃቀርይቀየር።  እስከ ቀበሌ ድረስ ወርዶ የክልል ድርጅቶች ይሁን ተቋማት ስራና እንቅስቃሴ የሚከታተል መንግስታዊ ተቋም ይፈጠር። በክልልና በመንግስት ደረጃ ኣለ የሚባለው ልዩነት የኣሰራር ሳይሆን የኣጠራር ነው። ኣንድነቱ የለም ካለም የመንግስቱ ባለስልጣን በክልል፡ የክልሉም ባለስልጣን በመንግስት ጉዳይ እጁ ረጅም ነው፡፣ ድርጅቱ ከመንግስት መንግስትም ከድርጅት የሚለያቸው መስመር የለም። ኣንዱ የሌላው ተቀጽላ ነው። እንዲህ ኣይነት ኣደረጃጀት ደግሞ ኣገር ኣይደለም የሚያገለግለው። ባለስልጣናትን ነው። ባለስልጣንን ያማካለ የኣገር ህልዉና (ኣንድነቱም ይሁን ልዩነቱ)ደግሞ በባለስልጣኑ የሚወሰን በመሆኑ ለኣደጋ የተጋለጠ ነው።በዚህ ሁለት ኣመታት የታየው ችግርም መንሳኤው ይሄው ነው፡ ስለዚህ ከዚህ ኣዙሪት ለመላቀቅ በድርጅታዊ መዋቅር ያልተካተተ በህግና በሃገር ለህግና ለሃገር የቆመ ሙያንበሙያውየሚኣስከብር ብሄራዊ ተቋሚትይፈጠሩ። ድርጅቶች የሚጠይቁት ሳይሆን ድርጅትን የሚጠይቅ በማንም የማይገፋ ለማንም የማይገፋ ከድርጅታዊ ወገንተኝነት ነጻ ሆኖ የሃገርን ህልዉና በበላይነት የሚጠብቅና የሚያስጠብቅብሄራዊ ተቋም ይቋቋም።መዋስ ካልቀረ (ፌደራሊዝሙን) ከነ ዉስጥ ቀሚሱ ነው።

ለብዙሃን ተገዙ የሚለዉ ሙግት (የሰላም ሃሳብ እንበለው) እግምት ዉስጥ ኣስገብቶ ስልጣን ኣብዘሃነት ብህዝብ ስም ዉህዳን ፈላጭ ቆራጮች እርካቡን የሚቆናጠጡበት መሰላል ነው። ግራ ዘመም ኣብዮት ባካሄዱ ኣገሮች እንደታየው። ስልጣኑን የሚያረጋግጠው ባላንጣዎቼ ናቸው የሚላቸው (ሃይል የነበራቸው ወይ ደግሞ ኣስጊ የሚላቸው)ዉህዳኑ የህብረተሰብ ክፍሎች እንደ ጠላት ፈርጆ  በማግለል፡ በመጨቆንና በማጥፋት ነው። ባለስልጣናቱ ለህዝብ ቆመናል የሚሉት(በኣፍም ቢሆን) ህዝቡ ለድህንነታቸው እስከቆመ ድረስ ነው።ወገንተኝነታቸው ዞሮ ዞሮ ለቡድናቸው ኣለያም ደግሞ ( በሰሜን ኮርያ ፡ በትግራይም እንበለዉ እንጂ እንደታየው) ለቤተሰባቸው ነው። ኣምባገነነት ጠላቱኣንድ ነው። ስልጣኑን የሚቀናቀነውን  ብቻ። ኣብዝሃነት ግን ጠላቶቹ ሁለት (በጠላት የፈረጃቸው ዉህዳኑና ብዙርያው የተሰባሰበን ኣብዘሃ ህዝብ) ናቸው። ዉህዳኑ የስልጣን እንቅፋት

ስለሚሆኑበት ብዙሃኑ ደግሞ ብስማቸው መነገዱን ስለሚያውቁበት።ስለዚህ ኣብዘሃነት(በጽንሰ ሃሳብም በተግባርም)በተለይም የስልጣን ዉክልና ኣስመልክቶ ብዙ ችግሮች የተጠናወቱት በመሆኑ ዳግም ይታይ። ይቀየርም።በዝቶም መብት ኣንሶም ኣንዲሁ መብት ነው የሚፈልገውና ለማንና እንዴት በሚለው ጽንሰ ሃሳብ ህዝቡ ይምከርበት ። ማርክሳዊ ር እዮተ ኣለምን መሰርት ያደርገው ኣሰራር በጣም የተለጠጠ ነው።

ብዙ ነን ብለው ብዙ ስለሚናገሩት ግን ትንሽ ልበል። ግንዛቤያቸው ኣዝብቶ ወደ ገደል ጫፍም እየወሰዳቸው ስለሆነ። ኣለክሳንደር (የመቄዶንያዉ) ኣለምን ለመቆጣጠር ሲከጅል ሃሳቡ እንጂ ሃገሩ ውይም ስልጣኑ ታላቅ ኣልነበረም። ራእዩ እንጂ ሃይል ኣልነበረዉም። ታላቅ ለመሆን የበቃዉ ታላቆችን ኣፍርሶ ነው። በጊዜው ግዙፍና ሃይለኛ የተባሉት ኣገሮችና ኣገረ ገዢዎችን ግጥሞ ነው። ሲጀምር ሃሳቡን ለኣማካሪዎቹ ኣካፍሎኣቸው ነበር። እዘምታለሁ ብሎ። ኣማካሪዎቹ ግን ኣልወደዱለትም። ብዙ ኣቅም (ሰራዊት) ሳይኖረዉ ሃያላን ኣገሮችን እንዴት እወራለሁ ይላል ብለው። ተግርመው (ደንግጠዉም እንበል) ኣነሱ በጣም ብዙ ናቸዉ ። ብዙ ጦርም ኣላቸዉ ኣትችላቸዉም ኣሉት። የሚያርፍ መስሏቸው።ኣለክሳንደር ግን የታየው የሱ ማነስ ኣይደለም። የነሱ በሽንፈት ሃሳብ መወረር ነው። እናም በመልሳቸው ተገርሞ (ተናዶም እንበል) “እኔንስ ምን ያህል ብትገምቱኝ ነው” ነበር ያላቸው። እንዳለዉም ኣልቀረም ግዙፎቹን ገጥሞ ኣለምን ሁሉ ( ብዙ ባይነገርለትም ከኢትዮጵያ በቀር)ለመግዛት በቅቷል። እራሱም ቢሆን ለሞት የበቃው እራሱ በወጠነው ትእቢት ነው። ትእቢት ጥሩ ኣይደለም። የሚያጠፋዉ ወዳጁን ነው። ፈርኦንን ማየት ነው።ነቡከደናጾርን ማየት ነው። ተመካሂዎቹ ከኢትዮጵያ ስለሆኑ ልዩ ኣያደርጋቸዉም። ልብ ማለት ጥሩ ነው ።ጎንደርም እኮ “ኣየጉ ኣየ ጉድ ብላታ ዳመና፡ ገዳዩ ደፊት ሟቹ ወደ ኋላ” ብሎታል ባንድ ኣጋጣሚ። ማስተዋል ጥሩ ነው።

እነዚህ ፖለቲከኞችየትግራይን ህዝብ ኢላማ ያደረገ ምጣኔ ሃብት ተኮር ክርክርም ኣላቸውና ስለዛም ትንሽ ልበል። ሙጉቱ ሃብታሞችነንና እኛ እንግዛ ነው ። የትግራይ ህዝብ ድሃ ስለሆነ መግዛት የለበትም ነው። ነገሩ ግራ ያጋባል። ግን ደግሞ መጠየቅ ተገቢ ነው።ህዝብ የማያውቀው በወርቅ የተነጠፈ መሬትወይም የተትረፈረፈ ሃብትካለ። በጎንደር ዉስጥድህነቱ ኣለ። በሸዋ ዉስጥ ኣለ። በኦሮምያም እንዲሁ። ሃብቱ የት ቢሄድ ነው? ፖለቲከኞቹ ለስልጣን ሲሉ (እንደሁሉጊዜ ኣመላቸው) ዋሸተውናል ማለት ነው።በመከባበርና በመፈቃቀድ ኣማራዉ ይሁን ኦሮሞው ትግራዩን ቢመራ ችግር የለዉም። ወገኑ ነው። ህዝቡ ነው።ይህ ደግሞ ኣዲስ ነገር ኣይደለም። ከዚህ በፊትም የሆነ ነው። በወረደ መውረድ ያስፈለገው ለምንድን ነው? በትግራይ ህዝብ ያላለፈ ስልጣንና ስልጣኔ የለም። ደሙም ያው ኣንድ ነው። ከትግራይ ህዝብ የተለየ ሆኖ ለመታየት ያሰፈለገው ለምንድን ነው? ህወሓት ኣቅም የለዉም፡ ኣምባገነን ነዉና ይውረድ ምክንያት ነው። ህወሓት ትግሬ ስለሆነ ኣይገዛም ግን መለክቱ ሌላ ነው። ስለዚህየፖለቲካ ክህደትና የሃሳብ ድህነት ኣንግቦበትግራይ ህዝብ ላይ ድል ለማስመዝገብ የሚጥርገድለኛ ኣማራ ወይም ኦሮሞፖለትኪኛ በዛም ኣነሰምስልጣን ኣይደለም የሚያስፈልገዉ። ሃኪም ነው።በመጀመርያ ራሱን እንዲያውቅ። ቀጥሎምእራሱን።

በኦሮምያ ክልል ብቅ ጥልቅ የሚለው የመገንጠል ጥያቄም ኣልባት ማግኘት ኣለበት። መገንጠልን የሚያቀነቅን የኦሮሞ የፖለቲካ ሃይል (ኣብላጫዉን ህዝብ ባይወክልም)ኣለ። የጥያቄው ፈርጥ ሃሳብ ደግሞ (በደሉ እንዳለ ሆኖ)ኢትዮጵያዉያንም ኣይደለንም ነው።በቅርቡ ከጣና ሃይቅ ኣካባቢ የተገኙ የበኩር ልጆች ለመሆናችው ማስረጃ ተገኘ ቢባልም የሚዋጠላቸው ነገር ኣልሆነም። ኢትዮጵያዊነት ለነሱ (መገንጠል ለሚያቀነቅኑቱ) ሱስ ሳይሆን የሚጠየፉት ሽታ ነው። የማታለያ ወጥመድ ነው። ልዩ ነን ብለው ስለሞያምኑ መጣን የሚሉት (ኣገር ባልጠፋ)ደግሞ በዉቅያኖስ ከተከበበዉ ማዳጋስካር ከሚባለው ደሴት ነው። እዉን የኦሮሞ ህዝብ ከማዳጋስካር የመጣ ነው? መቼ ነው የመጣዉ? ለምንስ ነው የመጣው? ማብራርያ ኣይሰጡም። መልሱ በድፍኑ ክዛው መጣን ነው። እነሱ ያሉት ይበሉ ለኔ የኦሮሞ ህዝብን እትዮጵያዊነት ጥያቄ ዉስጥ ማስገባትድፍረት ነው። በኔ ኣቅም የሚነሳም የሚለካም ኣይደለም። በሌላዉም ቢሆን እንዲሁ። የኦሮሞ ህዝብ ኢትዮጵያዊ ነት ጥያቄ የሚያስገባ ካለ ማንነቱ የሸጠ ወይ መጽሃፉን ለማጠብ የሚፈልግ ብቻ ነው። በኔ እድሜ እንኳን ይህ ህዝብ ለዚህች ኣገር የከፈለዉ መስዋእትንት ሳይ በጥያቄዉም በጠያቂዎቹም ግራ ነው የምጋባዉ። በተለይም በኦነግ/ኦህዴድ ተሰግስገው ቅኝነቱን በሚያቀነቅኑት።

የኦሮሞ የመገንጠል ፖለቲካ ኣቀንቃኞች ጥያቄ የቅኝ ሆነ ኣልሆነ ማወቅ ያለብን ሃቅ ኣለ። ጥያቄው የመብት ነው። ይህ ደግሞ ስደት ኣያስፈልገዉም ። ኢትዮጵያዊ ሆኖም መጠየቅ ይቻላል። መፍትሄ ሰጪው (ተወደደም ተጠላም) የኢትዮጵያ መንግስት

ነው። የኢትዮጵያ መንግስት ደግሞ ይሁንታዉን የሚሰጠው ህዝቡ የደገፈው እንደሆነ ነው። ህዝቡ ያመነበት እንደሆነ ነው። ድጋፉ ከነሳ ነጻነቱ አይታሰብም። ሩቅ መሄድ አያስፈልግም ሶማሊ ላንድ ማየት ነው። ታይዋንን ማየት ነው። መፍትሄው ያለው ባገር ዉስጥ እስከሆነ ደግሞ አማራጩ ከባላገሩ ጋር መነጋገር ነው። መወያየት ነው። መገንጠልን የሚያቀነቅኑት ግን ይህን አይወዱትም። ከአምሳ አመታት በኋላ ክርክራቸው መብት ተገፈፈ ሳይሆን ኢትዮጵያዉያን አይደለንም ነው። ላቲን ቋንቋ ተፈቅዶ (በቋንቋዉም እንዳይጽፍ ተከልክሎ የነበረ ነው): አስተዳድርም ተክልሎ(ኦሮሞ ቦኦሮሞ መተዳደር አለበት ተብሎ እስከ ትግራይ ድረስም የማስተድዳደር መብትም ተሰጥተው) አሁንም  የሚቀነቀነዉ ዜማ የቅኝ ተገዥነትን ነው። መገንጠል አለብን ነው። ይህ ደግሞ በመገንጠሉ ዙርያ የተሰባሰቡ በተወሰኑ የኦሮሞ ተወላጆች በየቀኑ የሚንጸባረቅ ሃቅ ነው።

ባእድ እንደሆኑ (የመገንጠሉ አቀንቃኞች) በግርድፉ ዋጡት እያሉን ስለሆነ ደግሞ መጠየቅ አለባቸው። ኢትዮጵያ የማነች? ተብለዉ። ጠጃሬ ሃይሉ ይባላል ሰዉየው። ይኖር የነበረው በትግራይ ዉስጥ ( ዓይባ ይባላል መንደሩ)  ማይጨው አካባቢ ነው። ጣልያን ኢትዮጵያን ወሮ የማይጨዉን አካባቢ እንደተቆጣጠረ  ከጠቋሬ ሃይሉ ጋር ይገናኙና "አገርህ የት ነው" ብሎ ይጠይቀዋል።የጣልያን ነገር። በጣልያናዊዉ ጥያቄ ተገርሞ ተናዶም "ምነዉ ተገላቢጦሽሆነ ነገሩ ከሮማ እዚህ ድረስ መጥተህ እንዴት ነው አገርህ የት ነው ብለህ የምትጠይቀው?"አለዉ።እንገንጠል ባዮቹ መጠየቅ ያለባቸው ደግሞ ይህ ነው። ከበአህር ማዶ መጣን ካላችሁ (እኔ ኣላልኩም) ኢትዮጵያዊዉን  አገርህ አይደለም የምትሉት እንዴት ነው? ተብለው።እትዮጵያ የኖረችዉ ከሰባት ሺ አመት በላይ ነው። የኦሮሞ ፍልሰት ኣጋጥሟል የሚባለው (በታሪክ) ቢሆነው አምስት መቶ ነው። እንግዲህ ሂሳቡ እናስላ ከተባለ በሸዋ፣ በወሎ ፣ በትግራይ በኦሮምኛ ተናጋሪ የተያዘመሬት በሙሉ የአማራዉ ነው። የአገው ነው። የትግራይ ነው። የደቡቡም የሶማሊዉም ነው ማለት ነው። ብዙ መሄድም ኣያስፈልግም።በከፋ ፣በሸዋ ብነ ካሌብ ጊዜ የተሰሩት ኣብያተ ክርስትያናት ማየት ነው። ጥንት የተጻፉ የታሪክ ማስረጃዎች ማገበብ ነው። ሳያስፈልግ ዘንዶዉን ጎርጉሮ ማውጣት ያስፈለገው ለምንድን ነው?

የመገንጠሉ አቀንቃኞች መገንጠልን ማቀንቀኑ ብቻ አይደለም ስህተታቸው። የትግል ስልታቸውም እንዲሁ ፈር የለቀቀ ነው። ከአንድ የነጻነት ታጋይ ነኝ የሚል የማይጠበቅ ነው። ድል ብለዉ የሚኩራሩበት ስልትና ተግባር ጎረቤታችው የሆነ የሌላዉን ክልል ተወላጅ የሆነውን ( ምንም የፖለትካ ተሳትፎ የሌለውን )በስመ አማራ፣ ትግሬ፣ ሱማሌ  ወዘተመግደል ነው። ማፈናቀል፣ በእሳት(በሰንዳፋ አካባቢ እንደተደረገዉ)ማቃጠል ነው።ጅውሃር እንዳለዉ በሜንጫ አንገቱን መበጠስ ነው። ኦሮቶዶክስ ክርስትያኑን ማሰቃየት ነው።ነው።ህዝቡ በደም ተሳሰሯል። ኣብሮ በልቷል። ኣብሮ ኑሯል። ኣብሮም ታግሏል። ይህ ትስስርና ስብጥር ኣልታይ ያላቸው ለምንድን ነው? ለምን በአኖሌ ጉዳና ይጓዛሉ?  ሃቁ እንነጋገር ከተባለ የኦሮሞ ህዝብ ትግል እዚህ ለመድረስ የበቃው የተቀረው የኢትዮጵያ ህዝብ ትግል ተጨምሮበት ነው። በመላ ኢትዮጵያ ህዝብ ትግል ነው። ኣስተዳደሩን ለምን ተቃወሙ፣ የመንግስት ተቋማት ላይ ለምን አሴሩ አይደለም ክርክሩ። በትግል ያለፈ ሁሉ ያደረገው ነው። ክርክሩ ለምን ህዝብን ይበድላሉ? ነው። ማስተዋሉን ይሰጣቸው። ሰጣቸውም አልሰጣቸውም ግን ማሳሰብያዬ በህወሓት ህወሓት (ማባበሉን አቁሞ ) ኦሮምያ ከገንጣዮች አዙሪት እንድትወጣበትኢትዮጵያም ሰላሟን እንድታገኝበት ዘላቂ መፍትሄ ማበጀት አለበት ነው።

የህግሓኤ (ሻእብያ) ነገርም መቋጨት አለበት።የኢትዮጵያ ሰላም ዋና ተቅናቃኝ ህግሓኤ ነው። ብየጊዜው ከሚከሰቱት ብጥብጦች በስተጀርባ የሻእብያ እጅ እንዳለ ጥርጥር የለዉም።  በትግራይ ህዝብ ሲፈጽም የመጣዉ ግፍም የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው። በተለያዩ ጊዜያት እያሰረገ የሚልካቸው ኣሸባሪዎች  ህዝቡን ከብቱን ጠልፈውና ዘርፈው በመዉሰድ ሰላሙን ነው እየነሱት ያሉት። በተለይ በድንበር አካባቢ ሂወትና ንብረት ሁሌም እንዳወደመ ነው። ወደብም መሬትም እየሰጠ ኢትዮጵያ የኢትዮጵያን ጠላቶች ሁሉ እንደደገፈ ነው። የቅርብ ተላላኪ (ኩልያቸው)፣ሚስጢር አቀባያቸው እሱ ነው። ስለዚህ ኢትዮጵያ በህግሓኤ እድሜ መራዘም የተጠቀመችዉ ነገር ቢኖር ሰላሟመደፍረስ ነው።እንደገና ነፍስ በዘራ ጠላት መታወክ ነው። ህግሓአኤ በራሱ ሂደት ይጠፋል የሚል የህወሃት መላምት አልሰራም። አይሰራምም። የበሬን ቆለጥ አንዲወድቅ እንደመጠበቅ ነው። ስለዚህ ህወሓት በህግሓኤ ያለዉ አቋም እንደገና መፈተሽ አለበት። አንዴ ጥፋት ስህተት ተሰርቷል፣ መደጋገሙ ግን ተገቢ አይመስለኝም።ለኤርትራን ህዝብ የማይጠቅም ነው። ኢትዮጵያን ወደ ጭቃ የሚከት ነው። ስለዚህ ሌላ ተልእኮ ከሌለ በስተቀር ክህግሓኤ ጋር ቅብብሎሽመጫወቱ ማብቃት አለበት። ጊዜው ደግሞ አሁን ነው።

የኣገው ህዝብ የመብት ጥያቄም መፍትሄ ማበጀት ኣለበት። የኣገው ህዝብና ታሪኩ ለቀባሪ ማርዳት ስለሆነ ብዙ ኣልልበትም። ኣንድ ነገር መታወቅ ያለበት ነገር ግን ኣለ። የኣገው ህዝብ ከሌሎች ክልሎች ያላነሰ የህዝብ ብዛት ኣለዉ። የራሱ መገበያያ ቋንቋ ኣለው። እራሱ ለማስተዳደርም ኣቅም ኣለው። ሞግዚት ኣይፈልግም።ማህጸኑ ኣስተዳዳሪዎቹን ማፍለቅ የሚችል ነው። በትግሉ ጊዜ ከማንም ያላነሰ ኣስተዋጾ ኣድርጓል።ተጨቁኖ ያለው ግን እሱ ነው። ብኣዴን በህወሓት ላይ እንዳይቆጣ ተብሎ። የኣማራ ክልል የመሬት ቆዳ ስፋት እንዳይቀንስ ተብሎ። ኣማራነት ለኣስተዳደር እንዲመች በተካለለ መሬት የምንሸጠዉና የምንለዉጠው ቢሆን ጥሩ ነበር። ግን ኣይደለም። ኣማራነት ወደድንም ጠላንም በልብና ከልብ የምነጋራዉ እሴት ነው። ኣገውነትም እንዲሁኣንድነት ነው። ልንከስረዉ የማይገባ ቅርስ ነው። በመሆኑም ቅርሱናን ታሪኩን ጠብቆ እንዲቆይ መብቱ ሊሰጠው ይገባል። እየተመናመነ የመጣዉ ህልዉናው መታደግ የሚቻለው መብቱየተከበረ እንደሆነ ነው። መብቴ ደግሞ ይከበር እያለ ነው። እራሴን ላስተድዳድር እያለ ነው። ስለዚህ ኢህኣዴግ ፖሊሲው ዳግም መፈተሽ ኣለበት። ግማሽ መብት የለም። ለሊላው ብሄረሰብ የተሰጠው መብት ለኣገዉም ይድረሰው። በህግ የተጠየቀን መብት በህግ መመለስ ግድ ይላል። ተገቢም ነው።

ሰንደቃላማዉም እንዲሁ ኣንድ ይበቃል። ለሎች ኣድረገዋል ብሎ መከተል ኣልፈየደንም።ሁሉ እይኮረጅን ኣንዘልቀዉም። ወይ ከኣኮራረጁ ኣለያም ከኣተግባበሩ እያበላሸነው ለችግር ነው የዳረገን። ጉዳቱ ደግሞ ኣያየነው ነው። የግድ መውለብለብ ኣለበት ከተባለም ቢጫ ቀይና ኣረንጓዴ ኣድርጎ ጥለት ወይም ኣርማ ቢጭመርበት መልካም፡፣ ያም ቢሆን ትርፍ ነው። ኣንዱን ሰንደቅ ኣላማ ብህዝብ ዉይይት ኣጽድቆ  እሱን ማዉለብለብ ይበቃል። እርግጠኛ ነኝ ባዳነት የሚሰማዉ የለም። እኩልነቱ ባንድ ኣገር ኣንድን ህዝብ የወከለ ከሰማንያ በላይ ሰንደቃላማ በማውለብለብ ኣይደለም የሚገለጸው። በተግባር ነው። ፍትህን በማስፈን ነው።ለዚች ባንዴራ ደሙን ያላፈሰሰ ኢትዮጵያዊ የለምና፡ ኣንድ በቂ ነው።በነባሩ እና በኣዲሱ ሰንደቃላማ ያለው ክርክርም እልባት ይሰጥበት። ህዝቡ እንደገና ይምከርበት። ካስፈለገም ድምጽ ይስጥበት።

ኮረምና ሮም ሆነንም ኣንዘልቀዉም። ኣንድ ብሄራዊ ቋንቋ ይኑረን ። እንደኔ ግእዝ ቢሆን እመርጣለሁ።  በታሪካዊነቱ፡ በብቃቱ እና የማንም ተጽእኖ የማይንጸባረቅበትና በህዝቡ ዉሳኔ የሚተገበር በመሆኑ። ከልብ ካለቀሱ እንባ ኣይገድም። ካልሆነ ደግሞ ኣማርኛዉም በኣግባቡ ይቀጥል። የስዊዘርላንዱ ኣይነት የቋንቋ ኣጠቃቀም (ሁለት ወይም ሶስት ቋንቋዎች ብሄራዊ የሚሆኑበት) በተግባር ቢዉልም ጉዳት ያለዉ ኣይመስለኝም። ብዙ ቋንቋ በማወቅ የተጎዳ የለም። ያዉም ኣገር በቀል። ዋናው ነገር ለመጣላትም ቢሆን የምንደማመጥበት ኣንድ ቋንቋ ይኑረን ነው። እንደ ህዝብም እንደ ምንግስትም በየ ክልሉ ኣስተርጓሚ ይዞ መሄድ ኣያዋጣም። ይህ ሲባል በድርጅቶች የበላይነት ወይም ዉስጣዊ ስምምነት የሚጸድቅና የሚፈርስ ቋንቋ ይኑር ኣይደለም የምለው። ህዝቡ የወሰነውን ነው። የሚነጋገርበት ህዝቡ ነውና መወሰን ያለበትም ህዝቡ ይሁን። በመንግስት/በድርጅት የተወሰነን ነገር ሁሌም ለችግር እንደ ዳረገን ነው።

ጭቅጭቅ፡ የርስበርስ ጦርነት፡ ለኢትዮጵያ ህዝብ ኣዲስ ኣይደለም። ጭቆናዉም ጭካኔዉም እንዲሁ። እዚህ የደረሰዉ እየተጣላ ፡ እየታረቀ፡ የጋራ ጠላት ሲመጣ ደግሞ ኣብሮ እየመከተ ነው።ልንኮራበት ይገባል። ልናውቀው ይገባል። ታሪካችን ብቻ ስለሆነ ሳይሆን የሚያስተምረንም ነገር ስላለ። በኣጼ ቴዎድሮስና በኣጼ ሚኒሊክ በኣጼ ተክለጊዮርጊስና በኣጼ ዮሃንስ ፡ በኣጼ ዮሃንስና በኣጼ ቴዎድሮስ፡ በኣጼዮሃንስና በኣጼ ሚኒልክ መሃል የነበረዉ ሹኩቻና ጦርነትስናስታዉስ ደግሞየሚለን ነገር ኣለ። ተዋግተዋል። ተዛምደዋል፡። ተዋልደዋል። በነገስታቱ መሃል የነበረው ሹኩቻ እዛው ተጀምሮ የሚያልቀውም እዛው ነበር። ኣገር ደግሞ ከሁሉ ይቀድማል።  ኣጼ ዮሃንስ ወደ ጎንደር ያቀኑት የሚኒሊክ ሴራ ጠፍቶኣቸው ኣይደለም፡ ኣገር ከሌለ ስልጣን፡ ኣገር ከሌለ ነጻነት የለም ብለው ነው።ኣሁን ግን ይህ ኣይደለም የምናየው። ህወሓት በድሏል ብሎ ህዝብን ካላጠፋሁ ብሎ የሚፎክር ነው ያለው። የህወሃት/ኢህኣዴግ ጥላቻ ስላለው ብቻ የኣባይን መሰራት (ከግብጽ ባላነሰ) የሚቃወም መኣት ነው፡፣ ሊያፈርስ በተላላኪነት የሚያገለግልም ኣለ። የሃገርን ታሪክ በወጉ ኣለማወቅ (እኔን ጨምሮ)ኣስተዋጽኦ እንዳለው መገመት ኣይከብድም፡ የተማርነው፡ የምንማረው ታሪክ የዉጭ ነው። የዉጭው ደግሞ የተሞላው (ታሪካችሁንና ባህላችሁን በተመለከተ) ካዱ የሚል ነው። ኣዲስ ጉዞ ይጀመር።

ባህል በተመለከተም በውጭ ባህል የሚኮራ ህብረተሰብ ነው እየተፈጠረ ያለውና ይስተካከል። ለመስፋፋቱ ዉጭ ኣገር ቆይቶ የሚመለሰው ኢትዮጵያዊ ትልቅ ኣስተዋጽኦ ቢኖረዉም መንግስትም ተገቢ ክትትል ባለማድረጉ ተጠያቂ ነው። ወጣቱ በባህሉ ተኮትኩቶ ማደግ ኣለበት። ግድ ደግሞ ይላል። ነገ ባለስልጣን፡ ወታደር፡ ወዘተ. ሆኖ ኣገርን የሚመራዉና የሚከላከለው እሱ

ነው። ስማቸው የረሳሁዋቸው አንድ የእትዮጵያ ኦርቶዶክስ ሃይማኖት አባት (ጳጳስ ናቸው) ያሉት ቁም ነገር አለ። የኢትዮጵያዊው ዘሎ ገባ ባህል ላይ ዘሎ መዘፈቁን ክንክናአቸዉ። በአሁኑ ጊዘ ያለዉ ችግር አሉ፡ "ፍረንጁ እግዚአብሄርን ለመምሰል፡ እቲጵያዊዉ ደግሞ ፍርረንጅን ለመምሰል መታከታችው ነው። ይህ ደግሞ የማይቻል ነገር ነው" ብለዋል። እዉነት ነው። ፈረንጅ ፈረንጅ ነው። ኢትዮጵያዊም እንዲሁ። ፋሽኑ ወርሶ፡ በሃሽሽና አደንዛዥ እጽ እራሱንአደንዝዞ ፈረንጅ ለመሆን የበቃ የለም። ትርፉ ልፋት ብቻ ነው። ስለሆነም ዜጋው ይህንን አውቆ በራሱ ባህል አንዲኮራ መነገር አለበት። በትምህርት መልክም መሰጠት አለበት። ሃላፊነቱ ደግሞ የመንግስቱ ነው። የህወሓትም ጭምር።

በመጨረሻ በአለክሳንደርና በዳዮጀነስ መሃል የነበረው የኑሮና የሃሳብ ልዩነት አስመልክቶ ታላቁ አለክሳንደርአለ የተባለዉን ጠቅሼ ጽሁፌን ላጠቃልል።ለህወሃት አመራሮች ጥሩ ጥሩውን እንዲያስቡ ፡ ታሪክ የሰጣቸውን ሃላፊነት እንዲገነዘቡ አቤቱታ መሆኑ ነው። ዳዮጀነስ በጠራራ ጸሃይ ፋኖስ አብርቶ ሰውን (እርሱ ሰዉ /አዋቂ የሚለዉን) ይፈልግ የነበረ ፈላስፋ ነው። ኪሮስ አለማየሁ "ሰብዶ የለይ"ብሎ እንደዘፈነው። የስነ ቁጡብነት (Stoicism) ፍልስልፍና አራማጅ ለህሊናዉ የሚያድር ገዳም አልባ መናኝ ፈላስፋ ነበር። ለተንደላቀቀ ኑሮ ግድ የሌለው ና የግል ንብረትም ብሆን መጠን እንዲኖረው የሚከራከር። አለክሳንደር ደግሞሃብት አግበስብሶ የማይጠግብ፡ስልጣን ወዳጅ፡አለምን ንብረቱ ያደረገንጉስ ነበር። በተወሰነ ደረጃም ቢሆን። ባጭሩ ዳዮጀነስ ለነፍስ፡ አለክሳንደር ደግሞ ለስጋ ያደረ ነው፡፣ አለክሳንደር የዳዮጀነስ ፡ ዳዮጀነስ ደግሞ የአለክሳንደርንኑሮአይሆነዉም። ያንዱ ሂወት የሚያብበው ሌላኛው ሲሻር ነው። "አለክሳንደር ባልሆን ኑሮ ዳዮጄነስን ነበር የምሆነዉ"ብሏል።ከቋመጡ አይቀር እንደአለክሳንደር ከተቆጠቡ አይቀር ደግሞ እንደ ዳዮጀነስ መሆን ግድ ይላል ማለቱ ነው። የህወሓት አመራርም መገንዘብ ያለበት ይህ ነው።በአንድነት ጉዞው ወይ ህዝቡን ወይ ስልጣኑን (ጥቅሙን) መምረጥ ይኖርበታል። ህዝብን እየበደሉ የህዝብ ነኝ ማለት የማይቻል ነው። ከመረጡ ደግሞ ፎቁ ሳይሆንለትውልድ የሚተላለፍ ስራን መስራትን ነው። መንግስትን የሚያቆይ ሳይሆን የሚቆይ መንግስትንመፍጠርን ነው። አቅፎ ደግፎ ለዚህ ያበቃዉን ህዝብ ነው። ዳዮጀነስ መሆን ነው።

ጎዲፍ ተፈሪ 03-30-18

እርማት፡ሃሳብና አስተያየት መስጠት ለምትፈልጉ

በ tgiorgis12@yahoo.comጻፉልኝ።

አመሰግናለሁ